በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ.ም.

አዲስአበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የድርጅቱ ራእይና ተልእኮ 1
የድርጅቱ ራእይ 1
የድርጅቱ ተልእኮ 2
የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሥልጣንና ተግባር 2
የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል 2
ድርጅታዊ መዋቅር 2
የሰው ኃይል 3
የፋይናንስ ምንጭ 3
የኦዲቱ ዓላማ 4
ለኦዲት የተመረጠው አካባቢ (Potential Audit Area) 4
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች 4
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 5
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 5
የግዢና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ /process description/ 6
ክፍል ሁለት 7
የኦዲት ግኝቶች 7
፩. የድርጅቱ የግዢ ሥርአት/አፈፃፀም የግዢ መመሪያን ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ፤ 7
የግዢ ዕቅድ መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ 7
በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በመለየት በጥቅል እንዲከናወን መደረጉን በተመለከተ 8
በድርጅቱ የግዢ መመሪያ መሰረት ግዥዎች መፈጸማቸውን በተመለከተ 9
የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለሚመለከታቸው ክፍሎች መድረሱን እና ክፍያው በአቅራቢው ስም መፈጸሙን በተመለከተ 10
ከኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ 11

የግዥ ሥራዎች ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ መደረጋቸውን በተመለከተ 12

፪. የድርጅቱ የንብረት አስተዳደር ሥርአት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ 13

እቃዎች ግምጃ ቤት ገቢ ከመደረጋቸው በፊት በሚመለከተው ባለሙያ እንዲረጋገጡ መደረጉን በተመለከተ 13

ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum& Maximum Stock Level/ መቀመጡን በተመለከተ 14

የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የተሟላ ማስረጃ የሚቀርብላቸው መሆኑን እና ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ መደረጉን በተመለከተ 16

የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ 17

ድርጅቱ የተሽከርካሪዎች ስምሪት መመሪያ ያለው መሆኑን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ 19

የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች የሚሰጡት አገልግሎት በየጊዜው እየተገመገመ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ 20

አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አቀማመጥ እና አወጋገድን በተመለከተ 21

፫. ድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 22

የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ከንብረት መዛግብት ከወጪ ቀሪ ጋር የሚታረቅ መሆኑን እና ልዩነት ሲኖር እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ 22

የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ የተደገፉ መሆናቸውን በተመለከተ 23

ክፍል ሶስት 24

መደምደሚያ 24

ክፍል አራት 28

የማሻሻያ ሃሳቦች 28

አባሪ 1፡ ድርጅታዊ መዋቅር 31

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 32

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በ1940ዎቹ መጀመሪያ የህዝብ ስራዎች ሚኒስቴር ሥር የውሃ ልማት ኤጀንሲ የሚባል ተቋም የተቋቋመ ሲሆን በአሜሪካ መንግስት እርዳታ “point four” በመባል ከተመሰረተው ተቋም ጋር በቅርበት ይሰራ ነበር ።

2. ግብጽ እና ሱዳን በየሀገሮቻቸው የአባይ ሸለቆ ጥናት በመጀመራቸው ኢትዮጵያም የአባይንና የሌሎች ወንዞች ተፋሰሶችን ለማጥናት ተጠሪነቱ ለህዝብ ሥራዎች ሚኒስቴር የሆነ የአባይ ተፋሰስ ጥናት የሚያካሂድ ክፍል ተቋቋመ። የውሃ ልማት ኤጀንሲ እና የአባይ ተፋሰስ ጥናት ተጠሪነታቸው ለህዝብ ሥራዎች ሚኒስቴር ሆኖ እስከ 1975 ዓ.ም ከቀጠሉ በኋላ በአንድነት የኢትዮጵያ ውሃ ልማት ባለስልጣን ተብለው ተጣመሩ። በመላ ሀገሪቱም ስምንት የውሃ ልማት ቀጠናዎች ተዋቀሩ። ይህ አደረጃጀት ለአራት አመታት ያህል ከቀጠለ በኋላ በ1979 ዓ.ም ብሄራዊ የውሃ ልማት ኮሚሽን በሚል እንደገና ተደራጀ። በዚህ ጊዜ የውሃ ልማት ባለስልጣን፣ የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 190/1980 ተቋቋሙ።

3. የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የነበረው በ1994 ዓ.ም የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ው.ሥ.ኮ.ድ) በሚል ስያሜ በድጋሚ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 156/1986 ተቋቋመ። ይህ የማቋቋሚያ ደንብ በደንብ ቁጥር 109/1996 አማካኝነት ለድርጅቱ ተጨማሪ ኃላፊነት እና ተግባር ተሰጥቶት ማሻሻያ ተደርጎበታል። በማሻሻያው ተጠሪነቱ ለውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሲሰጥ የተፈቀደለት ካፒታልም ከሁለት መቶ አስራአንድ ሚሊዮን ሶስት ሺ ብር ወደ ሶስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሺ ብር አድጓል። ድርጅቱ የመጠጥ ውሃ ፣ የግድብና መስኖ፣ የመንገድ፣ የደረቅ ወደብ ፣ የህንፃና ሌሎች የተለያዩ ግንባታዎችን ያካሂዳል።

የድርጅቱ ራእይና ተልእኮ

የድርጅቱ ራእይ

4. በ2015 ዓ.ም በምስራቅ አፍሪካ በውሃ እና በሌሎች የግንባታ ስራዎች ቀዳሚ እና ተመራጭ ኮንስትራክሽን ድርጅት ሆኖ ማየት።

የድርጅቱ ተልእኮ

5. ብቃት ያለው የሰው ሀይል እና ዘመናዊ መሳሪያዎች በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ የግድብ ፣ የመስኖና ድሬኔጅ፣ የመጠጥ ውሀ፣ የሀንፃ የኃይል ማመንጫ፣ የኤሌክትሮ መካኒካልና ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎች በማከናወን ከአገልግሎቱ ከሚሰበሰበውና ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ተመሳሳይ የልማት ስራዎችን በአገሪቱና በሌሎች አገሮች በማስፋፋት ሀገሪቱን በውሃ ሀብቷ ተጠቃሚ ማድረግ።

የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሥልጣንና ተግባር

6. ድርጅቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 156/1986 እና የማሻሻያ ደንብ ቁጥር 109/1996 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባር ተሰቶታል፡-

- የውሃ ሀብትን ለማልማት የሚሰሩ የግድብ ስራዎች፣ የመሰኖ ስራዎችን፣ የውሃ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎችን የመጠጥ ውሃ ማከፋፈያ መስመሮችን፣ የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮች ስራዎችን፣ የድሬኔጅ ስራዎችን፣ የጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ስራዎችን፣ የሪክላሜሽን ግንባታዎችን፣ የወንዝ መከለስ ግንባታዎችን፣ የመንገዶችና የሕንጻ ግንባታዎችን ማከናወን፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ስራዎችን ማካሔድ፤
- የውሃ ሀብትን ለመስኖ እርሻና ተጓዳኝ ስራዎች ልማት ለማዋል የሚያስችሉ ግድቦችን በባለቤትነት ይሰራል፣ ያስተዳድራል፣ ለግንባታ ያወጣውን ወጪ ከተጠቃሚዎች በመሰብሰብ ገንዘቡን ለተመሳሳይ ልማት ያውላል፤
- ቦንድ ያወጣል፣ ይሸጣል፣ በዋስትና ያስይዛል፤
- በተጓዳኝ ለስራው የሚየስፈልጉትን የተለያዩ ቧንቧዎችን ሊያመርትና ሊሸጥ ይችላል።

የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

7. የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ለመማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት በሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እንዲኖረው ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ የመሳሪያዎች አመራር ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮንስትራክሽን ሥራ አመራ ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮርፖሬት ፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ እና የሰው ሀብት ሥራ አመራርና ድርጅታዊ ልማት ሥራ አስፈጻሚ፣ ኮርፖሬት

ፕላኒንግ የሥራ ሂደት፣ የኦዲት አገልግሎት የሥራ ሂደት፣ ኮርፖሬት ሥነ ምግባር መከታተያ የሥራ ሂደት፣ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች የሥራ ሂደት፣ የህግ አገልግሎት የሥራ ሂደት እና የለውጥ የሥራ አመራር የሥራ ሂደት ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ (የድርጅቱ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡)

የሰው ኃይል

8. ድርጅቱ 672 ቋሚ እና 763 ኮንትራት በድምሩ 1435 ሠራተኞች እንዲኖረው በመዋቅር የጸደቀለት ቢሆንም ሰራተኞችን በኮንትራት ለመቅጠር ካስፈለገው በመዋቅሩ ያልተገደበ ሲሆን እስከ በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም ያለው የሰው ኃይል ቋሚ ወንድ 513 ሴት 159 ድምር 672 እንዲሁም ኮንትራት ወንድ 1298 ሴት 180 ድምር 1478 በጠቅላላው ወንድ 1811 ሴት 339 በድምሩ 2150 ቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

9. ድርጅቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 156/1986 እና የማሻሻያ ደንብ ቁጥር 109/1996 መሰረት የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ከልዩ ልዩ የግንባታ ሥራዎች ከሚያገኘው ገቢ የሚመደብለት ሲሆን ከ2002-2005 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ካፒታል የተመደበው በጀት እና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት		ተፈቀደ በጀት	ስራ ላይ የዋለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ
2002	መደበኛ	67,498,169.00	27,606,123.61	40.90%
	ካፒታል	3,175,791,830	119,442,093.63	3.76%
2003	መደበኛ	91,080,849.00	95,672,368.00	105.04%
	ካፒታል	3,948,274,038	1,651,995,402	41.84%
2004	መደበኛ	132,719,008	121,639,205	91.65%
	ካፒታል	5,372,420,953	3,066,207,992	57.07%
2005	መደበኛ	52,696,377	30,772,305	58.40%
	ካፒታል	4,610,297,385	1,876,287,167	40.70%

የኦዲቱ ዓላማ

10. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በመመሪያው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን እና ተመጋጋቢ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ለመገምገም ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ በድርጅቱ ላይ የሚታዩ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን እና መንስዔዎቻቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለኦዲት የተመረጠው አካባቢ (Potential Audit Area)

11. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) የኢትዮጵያ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

12. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን በሁለተኛው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም:-

    1. የድርጅቱ የግዥ ሥርዓት አፈጻጸም የግዥ መመሪያን ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

    2. የንብረት አስተዳደር አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፤

        2.1 የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

        2.2 የንብረት አወጋገድ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

    3. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

13. ከላይ ለተመረጡት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና ሁለት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 40 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criterias) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው የተስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ፤ የሥራ መመሪያ እና ደንቦች፣ በድርጅቱ የተጠናው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም የመረጃ ድህረ ገጾች/web site/ ናቸው፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

14. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002-2005 ያሉትን የአራት በጀት ዓመታት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

15. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት እና በናሙና በተመረጡ የተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት፣ የከሰም ግድብና መስኖ ልማት እንዲሁም ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከድርጅቱ የግዥና የንብረት አስተዳደርና አፈጻጸም ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ እና ንብረቶችን ባሉበት ቦታ ተገኝቶ በአካል በማየት ነው፡፡

የግዢና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ

/process description/

የግዢ ፍላጎት ማዘጋጀት
/Need Assessment/

የግዢ በጀት ማዘጋጀት
እና ማጸደቅ

የግዢ ዕቅድ ማዘጋጀት

የግዢ ጥያቄ ማቅረብ እና
መስፈቀድ

የግዢ መመሪያ በሚፈቅድ መንገድ
አቅራቢዎችን መጋበዝ ለግዢ

ከአሸናፍው አቅራቢ ድርጅት
ግዢ መፈጸም

ንብረቶቹ በስፔስፊኬሽን መሰረት
ስለመግዛታቸው ከተረጋገጠ በኃላ
ተጣርቶ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ

የንብረት ወጪ ጥያቄ ማቅረብ
እና ማስፈቀድ

ንብረቱን ወጪ ማድረግ

ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር መስጠት
እንዲሁም ለተሽከርካሪዎች እና
መሽነሪዎች ቋሚ ፋይል ማዘጋጀት

አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ
በአወጋገድ መመሪያ መሰረት
ማስወገድ

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

፩. የድርጅቱ የግዢ ሥርአት/አፈፃፀም የግዢ መመሪያን ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ፤

የግዢ ዕቅድ መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

16. በድርጅቱ ግዥ እንዲያከናውኑ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች በቅድሚያ የግዥ እቅድ በማዘጋጀትና የግዥ ስልት በመለየት በወቅቱ የተፈለገውን ግዥ በማከናወን፣ የዋጋ ቅናሽና የጥራት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡

17. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ ዕቅድ እንደማይዘጋጅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

18. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የሎጂስቲክስ ንዑስ የስራ ሂደት የሥራ ኃላፊዎች፣የመሳሪያዎች አስተዳደር የግዥ ቡድን የሥራ ኃላፊዎች እና የየፕሮጀክቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በድርጅቱ ግዥዎች በዕቅድ ሲከናወኑ እንዳልነበረ፣ ይህም የሆነበት ምክንያት ከእያንዳንዱ ክፍል የተጠቃለለ ዓመታዊ የግዥ እቅድ ተዘጋጅቶ ለግዥ ክፍል ባለመላኩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

19. በድርጅቱ መከናወን ያለባቸው ግዢዎችን በቅድሚያ ተለይተው ቢያንስ በየሩብ አመቱ የሚፈለጉ የእቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች በመለየት የግዢ እቅድ በማዘጋጀት በዕቅድ አለመመራቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው እና የማይሰጣቸው ግዢዎች በቅድሚያ ባለመለየታቸው አጣዳፊ የሆኑ እቃዎች ሳይገዙ ሌሎች ለረጅም ጊዜ የሚፈለጉ እቃዎች ላይ ገንዘብ እንዲወጣ ሊያደርግ እና ለግንባታ ስራ በአጣዳፊ የሚፈለጉትን እቃዎች እንደ ነዳጅ፣ መለዋወጫ፣ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላይ እጥረት እንዲፈጠር እና በዚህ ምክንት ሥራ እንዲቋረጥ እና እንዲጓተት ሊያደርግ ይችላል፡፡

በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በመለየት በጥቅል እንዲከናወን መደረጉን በተመለከተ

20. በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በቅድሚያ በመለየት በጥቅል እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡ የፕሮፎርማ ግዥ ለመፈጸም ሲባል በጥቅል ሊገዙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍሎ መግዛት አይገባም፡፡

21. በናሙና በታዩት በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ በከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች፡-

- ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት በፕሮጀክቱ የተፈጸሙ ግዢዎች በናሙና በታዩበት ወቅት አልፎ አልፎ ግዥዎች በመከፋፈል የሚፈጸሙ መሆኑን፣
- ከሲሚንቶ፣ ብረት እና ነዳጅ በስተቀር በድርጅቱ በርካታ ለኮንስትራክሽን የሚያገለግሉ እቃዎች በጥቅል የማይገዙ መሆኑን፣
- በፕሮፎርማ መገዛት የሚገባቸው ግዥዎች አልፎ አልፎ ከተለያዩ ድርጅቶች ቢያንስ ከሶስት አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ ከአንድ አቅራቢ ብቻ በተገኘ ፕሮፎርማ ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፣
- ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት በተንዳሆ፣ በከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ በፕሮጀክቶች የተፈጸሙ ግዢዎች በናሙና በታዩበት ወቅት አልፎ አልፎ ግዥዎች ከግዥ ጣሪያ በላይ እንደሚፈጸም፣

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው የታዩት የተንዳሆ፣ የከስም ግድብና መስኖ ልማት እና የሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡

- ከዋና መ/ቤት ለፕሮጀክቶች የአቅርቦት እጥረት በሚኖርበት ጊዜ ፕሮጀክቶች በራሳቸው ግዥ ስለሚፈጽሙ ግዥዎች በመከፋፈል እንደሚፈጸሙ፣
- ግዢው በጣም አስቸኳይ በሚሆንበት ጊዜ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ከግዥ ጣሪያ በላይ ግዥ እንደሚፈጸም፣
- አቅራቢዎች ከእስቶክ የለንም በሚሉበት ወቅት እና ከስቶክ የሌላቸው መሆኑን out of stock የሚል ከአቅራቢዎቹ በማስመታት ከአንድ አቅራቢ እንዲገዛ የሚደረግ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

23. ይህንንም በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የሎጂስቲክስ ንዑስ የሥራ ሂደት እና የመሳሪያዎች አስተዳደር የግዥ ቡድን የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣

- ❖ ግዥ በዕቅድ ስለማይመራ ከፋፍሎ የመግዛት ሁኔታዎች እንዳሉ፣
- ❖ አቅራቢዎች ከእስቶክ የለንም ሲሉ ከስቶክ እንደሌላቸው out of stock ማህተም እንዲመቱላቸው አቅራቢዎቹ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ቃለ-ጉባኤ በመያዝ ግዢ እንደፈጸሙ፣
- ❖ በ2003 በጀት ዓመት ግዥዎች ከግዥ ጣሪያ በላይ ሲፈጸሙ እንደነበር፣

ገልጸዋል፡፡

24. በጥቅል ሊገዙ የሚገባቸው ግዥዎች ተከፋፍለው እንዲገዙ መደረጉ እና ከግዢ ጣሪያ በላይ ግዢዎች መፈጸሙ ድርጅቱ ለቁጥቁጥ ግዥ እንዲጋለጥ እና በየወቅቱ ለሚከሰተው የዋጋ ንረት ተጋላጭ በመሆን ተደጋጋሚ ግዥ በመፈጸም ጊዜና ገንዘብ ማባከንን ከማስከተሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት እና የተዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ ከጅምላ ግዥ ሊገኝ የሚችለውን የዋጋ ጠቀሜታ ማግኘት አያስችለውም፡፡

በድርጅቱ የግዢ መመሪያ መሰረት ግዥዎች መፈጸማቸውን በተመለከተ

25. በድርጅቱ የሚፈፀሙ ግዢዎች በድርጅቱ የግዢ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን የግዢ ስልቶች መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ የግዥ ስልቱም የተመረጠበት ምክንያት ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ ሊጸድቅ ይገባል፡፡

26. በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ፣ በተንዳሆ እና ከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግዥዎች ሲፈጸሙ አቅራቢዎች ትክክለኛ ብቸኛ አቅራቢ ስለመሆናቸው በጥናት ሳይረጋገጥ ግዥ አልፎ አልፎ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ግዥ እንደሚፈጸም በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የሎጀስቲክስ ንዑስ የስራ ሂደት ቡድን የሥራ ኃላፊዎች፣ የመሳሪያዎች አስተዳደር የግዥ ቡድን የሥራ ኃላፊዎች እና የየፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ብቸኛ አቅራቢ የሚባሉት በትክክል ብቸኛ አቅራቢ ስለመሆናቸው በድርጅቱ በጥናት ባይረጋገጥም እቃዎቹን የማቅረብ ውክልና ምስክር ወረቀት /Certificate of

Authorized Agent/ ስላላቸው እንደብቸኛ አቅራቢ ታይተው ግዥ ከአቅራቢዎቹ ሲከናወን የነበረ መሆኑን፤ አሁን ግን ብቸኛ አቅራቢዎች ተጠንተው ለውሳኔ ለማኔጅመንት የቀረበ መሆኑን እና እንደጸደቀ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

28. በድርጅቱ የግዢ አስተዳደር መመሪያ ላይ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፉ ወይም አገልግሎቱ ከአንድ ብቸኛ አምራች፣ አስመጪ ወይም ከአንድ የተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ የሚገኝ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማያስፈልግ ወይም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዢን ይፈቅዳል ሆኖም ብቸኛ አስመጪ ወይም አቅራቢ መሆኑ በጥናት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ሳይሆን ከአንድ አቅራቢ ግዥን መፈጸም ሌሎች አስመጪ ወይም አቅራቢ ድርጅቶችን የማያሳትፍ እና ግዥው ያለጨረታ እንዲፈጸም ከማድረጉም በላይ በአቅራቢዎች መካከል ትክክለኛ የውድድር መንፈስ እንዳይኖር ብቸኛ አቅራቢዎች የተባሉት ለዕቃዎች የፈለጉትን የዋጋ ተመን እንዲጥሉ እና ኢኮኖሚያዊ ያልሆነ ግዥ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡

የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለሚመለከታቸው ክፍሎች መድረሱን እና ክፍያው በአቅራቢው ስም መፈጸሙን በተመለከተ

29. በድርጅቱ ግዥን የሚፈቅዱና የሚያጸድቁ በግዥ መመሪያ መሰረት ሥልጣን የተሰጣቸው ኃላፊዎች የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲልኩ ኮፒዉ ለንብረት ክፍል፣ ለግዥ ክፍል እና ለመሳሰሉት ክፍሎች ሊደርስ እንዲሁም ክፍያው በአሸናፊው አቅራቢ ስም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

30. በድርጅቱ ተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ፕሮጀክቶች የእቃዎች ግዢ የሚፈጸሙት ከአዲስ አበባ ሲሆን ለሚፈጸሙአቸው ግዢዎች ለክፍያ ይረዳ ዘንድ የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለፋይናንስ የሚደርስ ቢሆንም ቼክ የሚዘጋጀው ግን በአቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያዎች ስም በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ እስከ ብር 400,000.00 በግዢ ባለሙያዎች ስም የሚዘጋጅ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ስለጉዳዩ የድርጅቱ ኮርፖሬት ፋይናንስ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የግዥ መመሪያቸው እንደማይፈቅድ ለወደፊቱ ድርጅቱ አዲስ የአሰራር ስርዓት እየተገበረ ስለሆነ ግዥዎች ሁሉ በማዕከል ደረጃ የሚከናወኑ ስለሚሆን የተከሰተው ችግር ይቀረፋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

32. በድርጅቱ ለሚፈጸሙት ግዥዎች ክፍያ ሲፈጸም ቼክ ባሸነፈው አቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያዎች ስም ማዘጋጀቱ የድርጅቱን የግዥ መመሪያ ከመጣሱ በተጨማሪ ለጥፋት እና ለብክነት በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

ከኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

33. ድርጅቱ በኪራይ ከሚያሠራቸው መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ማግኘቱን ሥራው በሚመለከታቸው የቅርብ ኃላፊዎች ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግና በየወሩ ለዋና መ/ቤት ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡ ድርጅቱ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች በኪራይ ከመጠቀሙ በፊት አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ሊሰራ ይገባል፡፡

34. በተንዳሆ እና ከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በኪራይ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሰሩበት ሰዓት ምዝገባ የሚከናወነው በሳይት ላይ በሚገኝ የቀን ሰራተኛ ሲሆን የኪራይ ገልባጭ መኪናዎች ምልልስ እና መሳሪያዎች የሰሩበት ሰዓት በብጣሽ ወረቀት ላይ የሚመዘገብ መሆኑ ታውቋል፡፡ የኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላልሰሩበት 2437.33 ሰዓት በአማካይ የክፍያ ስሌት መሰረት ብር 4,387,194.00 በላይ ክፍያ እንደተፈጸመ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የኪራይ ማሽነሪዎች ክፍያ ሰነድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. ከዚህም በተጨማሪም የመሳሪያ ኪራይ እንደመጨረሻ አማራጭ ተወስዶ በቀን አንድ ገልባጭ መኪና ሊገዛ የሚችል ገንዘብ ለኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ወጪ ከመደረጉ በፊት በድርጅቱ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ እንዳልተሰራ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

36. ስለጉዳዩ በድርጅቱ የግድብ፣ መስኖ እና መንገድ ኮንስትራክሽን ንዑስ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቀን ሰራተኛ የየቀኑን የኪራይ ገልባጭ መኪናዎች ምልልስ እና መሳሪያዎች የሰሩበትን ሰዓት የመዘገበውን በሰዓት ፎርም/Time Sheet/ ላይ ከተገለበጠ በኃላ በምህንድስና ክፍል ጸድቆ ለክፍያ እንደሚላክ፣ ነገር ግን ስህተቶች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ክትትል ሊደረግባቸው ይገባ እንደነበር ለወደፊቱ ግን እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ በኪራይ መሳሪያዎች ሰዓት አያያዝ ላይ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል በማለት ገልጸዋል፡፡

37. በተጨማሪም በድርጅቱ የግድብ፣ መስኖ እና መንገድ ኮንስትራክሽን ንዑስ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ እስከ 1996 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ድርጅቱ በራሱ መሳሪያዎች የግንባታ ሥራ ይሰራ

እንደነበር በ1997 ዓ.ም መንግስት ትላልቅ የመስኖ እና ግድብ ግንባታ ሥራዎች ለድርጅቱ ስለተሰጡ ባሉት መሳሪዎች እነዚህን ፕሮጀክቶች በተባለበት ጊዜ ለማጠናቀቅ ስለማይቻል ወደ ኪራይ መገባቱን፣ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ድርጅቱ ቆም ብሎ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ አለመስራቱን ገልጸዋል፡፡

38. በድርጅቱ የኪራይ መሳሪያዎች የሰሩበት ሰዓት በቀን ሰራተኛ ከመሞላቱም በላይ በስራ ላይ የዋለው ሰዓት የሚመዘገበው በብጣሽ ወረቀት በመሆኑ እና ስለትክክለኛነቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ባለመዘረጋቱ በሰዓት ከብር 700 እስከ ብር 2900 ድረስ የሚከፈልባቸውን መሳሪያዎች አለአግባብ የሰዓት ጭማሪ በማድረግ ድርጅቱ ላላገኘው ጥቅም ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጣ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ በድርጅቱ ለኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በ2003፣ 2004 እና 2005 በጀት ዓመት ብር 174,500,362.35፣ ብር 432,349,783.00 እና ብር 697,594,994.21 እንደቅደም ተከተሉ ለኪራይ ወጪ ሆኗል፡፡ ይህም በቀን ሲሰላ ብር 476,776.95 ፣ ብር 1,181,283.56 እና ብር 1,905,997.25 እንደቅደም ተከተሉ ወጪ መደረጉን ያሳያል ይህም በትንሹ አንድ ገልባጭ መኪና ለመግዛት የሚያስችል ሂሳብ ነው፡፡

39. ድርጅቱ በቀን ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ መኪኖች ወጪ ከማድረጉ በፊት በኪራይ መኪኖች ከመጠቀም እና በረጅም ጊዜ ብድር መኪኖችን ከመግዛት ወይንም የፋይናንስ ሊዝ በማመቻቸት ከሊዙ በኋላ የእርጅና ዋጋን በመክፈል መኪኖቹን የራሱ ንብረት ከማድረግ የትኛው አዋጭ እንደሆነ ተገቢውን ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ያለማድረጉ ድርጅቱ ትርፋማ ሆኖ የራሱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች እንዳይኖሩት ከማድረጉም በተጨማሪ በኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

የግዥ ሥራዎች ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ መደረጋቸውን በተመለከተ

40. በድርጅቱ ፕሮፎርማ መሰብሰብና ማጠቃለያ ወይም ግምገማ የማከናወን፣ ግዥን ማከናወንና ርክክብ የማድረግ፣ የገቢ ደረሰኝ የማዘጋጀትና ሰነድ የማረጋገጥን እንደ አግባብነታቸውና የጠቀሜታ ደረጃቸው እየታየ ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ ፕሮፎርማ መሰብሰብ እና ግዥውን የመፈጸም ሥራ የሚሰራው በአንድ ግዥ ባለሙያ መሆኑን፣ ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ ገቢ የማድረግ

እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ንብረቶቹን ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በአንድ ንብረት ያዥ ሰራተኛ እንደሚሰራ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የሎጅስቲክስ ንዑስ የስራ ሂደት ኃላፊዎች፣ የመሳሪያዎች አስተዳደር የግዥ ቡድን መሪ እና የየፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው መሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት/BPR/ ትግበራ በኃላ የተከሰተ የአሰራር ስህተት ቢሆንም ድርጅቱ አዲስ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ እያደረገ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የሚስተካከል ይሆናል በማለት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

43. በድርጅቱ የግዥ ኘሮፎርማ መሰብሰብ እና ግዥውን የመፈጸም ሥራ በአንድ ግዥ ባለሙያ እንዲፈጸም መደረጉ እና ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ ገቢ የማድረግ እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ንብረቶቹን ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በአንድ ሰራተኛ እንዲሰራ መደረጉ የሥራ ክፍፍል /segregation of duties/ እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ ለስርቆት፣ ለብክነትና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

፪. የድርጅቱ የንብረት አስተዳደር ሥርአት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

እቃዎች ግምጃ ቤት ገቢ ከመደረጋቸው በፊት በሚመለከተው ባለሙያ እንዲረጋገጡ መደረጉን በተመለከተ

44. ድርጅቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኛቸውን ቋሚና አላቂ እቃዎች ሲረከብ በእስፔሲፊኬሽናቸው መሰረት መሆናቸው በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ እና አስፈላጊው ምዝገባ መከናወን ይገባዋል፡፡

45. በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ንብረቶች ተገዝተው ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው መገዛታቸው በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማን (MAN) ለተባለ ገልባጭ መኪና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጥቶ የተገዙት 12 የፊት እና 12 የኂላ በድምሩ 24 ባሌስትራዎች (Leaf Springs) ለመኪናው የማይሆን በመሆኑ ከሁለት ዓመት በላይ በግምጃ ቤት የተቀመጠ መሆኑን በመስክ ኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. ይህንንም በተመለከተ የከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሥራ ኃላፊዎች ስለተገዛው ባሌስትራ (Leaf Spring) ተጠይቀው በሰጡት መልስ ያለአግባብ የተገዙት ባሌስትራዎች እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ለዋና መ/ቤት ሪፖርት ቢደረግም እርምጃ አለመወሰዱን ገልጸዋል፡፡

48. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የሎጀስቲክስ ንዑስ የስራ ሂደት ኃላፊዎች፣ የመሳሪያዎች አስተዳደር የግዥ ቡድን መሪ እና የፕሮጀክቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እቃዎች ተገዝተው ሲመጡ በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት ተገዝተው ስለመምጣታቸው በንብረት ገቢ ማድረጊያ ቫውቸር ጀርባ ያረጋገጠው ባለሙያ የሚፈርም ቢሆንም እንደአሰራር የሚገዙ ንብረቶች በትክክል በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው ስለመገዛታቸው የሚረጋገጥበት አሰራር ሥርዓት እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ በነበረው የአሰራር ስርዓት የተከሰተ የአሰራር ችግር ቢሆንም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ዓይነት የአሰራር ችግር እንዳይከሰት ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

49. በድርጅቱ ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው ስለመገዛታቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ጥራታቸውን ያልጠበቁ እና ለሚፈለገው ዓላማ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎች በመገዛታቸው ዕቃዎች ለተባለለት ዓላማ ሳይውሉ ድርጅቱን ለብክነትና ለኪሳራ ይዳርጋሉ፡፡

ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum& Maximum Stock Level/ መቀመጡን በተመለከተ

50. የድርጅቱ ዕቃዎች በድርጅቱ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ እንደእንቅስቃሰያቸው ፍጥነት፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው ሊያዙና ሊቀመጡ ይገባል፡፡ በክምችት የሚያዙ እና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & Maximum Stock Level/ ሊቀመጥላቸው እና በዚያው መሰረትም የንብረቶች/ እቃዎች/ ክምችት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

51. በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች፡-

- በንብረት መጋዘን ውስጥ እቃዎች እንደ እንቅስቃሴያቸው ፍጥነት፣ አዲስ፣ የሚያገለገሉ፣ የማያገለግሉ፣ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ ያልተደረገ መሆኑን፣

- ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በክምችት ሊያዙ የሚገባቸው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & maximum Stock Level/ እንዲኖራቸው ያልተደረገ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ንብረቶችን እንደተፈጥሮ ባህሪያችው እንዲያዙና እንዲቀመጡ በማድረግ ረገድ ክፍተቶች ቢኖሩም የሚያገለግሉ ንብረቶች ከማያገለግሉ ጋር ተቀላቅለው እንዳይቀመጡ በካይዘን አሰራር ፍልስፍና መሰረት የተሰሩ ጅምር ስራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የየፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች ግን ንብረቶችን በተባለው መሰረት እንዲቀመጡ አለመደረጉን ይህንን ለማድረግም የመጋዘን እጥረት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

53. በተጨማሪም በክምችት ሊያዙ የሚገባቸው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & Maximum Stock Level/ እንዲኖራቸው ተደርጎ አለመጠናቱን የቃሊቲ ቅርንጫፍ የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ እና የየፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

54. በዋናው መ/ቤት ቃሊቲ ቅርንጫፍም ሆነ በፕሮጀክቶች ግምጃ ቤቶች ውስጥ በክምችት ለሚያዙ እና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ላላቸው ንብረቶች /ዕቃዎች/ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum and Maximum Stock Level/ እንዲቀመጥላቸው ካልተደረገ ድርጅቱ በየጊዜው ለግንባታ የሚፈልጋቸው እንደ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ ነዳጅ፣ መለዋወጫ እና ለሎች ዕቃዎች በሚፈለጉበት ወቅት በተፈለገው መጠን በመጋዘን ውስጥ እንዲገኙ ካልተደረገ ስራን ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡ በክምችት የሚያዙ እቃዎች እንደ እንቅስቃያቸው ፍጥነት፣ አዲስ፣ የሚያገለግሉ፣ የማያገለግሉ፣ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ ካልተደረ ለብልሽት ሊዳረጉ፣ አዲስ የተገዙት እና አገልግሎት የሚሰጡ ከማያገልግሉ ጋር ተቀላቅለው ሲቀመጡ ለብክነት እና ለስርቆት ሊጋለጡ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህርያችው ካልተያዙ ከመበላሸታቸው በተጨማሪም በአካባቢ እና በሰው ልጅ ጤንነት ላይ ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የተሟላ ማስረጃ የሚቀርብላቸው መሆኑን እና ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ መደረጉን በተመለከተ

55. የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች በንብረት መጋዘን ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት ተገቢው የገቢ እና የወጪ ማስረጃዎች ሊሟላላቸውና በሚመለከተው ኃላፊ ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የድርጅቱ ንብረቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወጪ ከተደረጉ በኋላ በትክክል ለታቀደው ዓላማ የዋሉ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

56. በተንዳሆ እና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሚንቶዎች፣ ብረቶች እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ከንብረት ክፍል በአንድ ፎርማን በጥቅል ወጪ ከተደረጉ በኋላ ሳይት ላይ ላሉት ለሌሎች ፎርማኖች የጠየቁትን ያህል ያለምንም መተማመኛ/ሰነድ የሚታደል ሲሆን ለፎርማኖች ስንት እንደታደለ እና ስንት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣ ከመጋዘን በጥቅል ወጪ የተደረገው የሲሚንቶ፣ ብረት እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ በትክክል የዋሉ መሆኑ የሚታወቅበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

57. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ጥቅምት 9 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገው የሥራ ጉብኝት፡-

- በአቅርቦት ቁጥጥር ክፍል የሚያዘው የሲሚንቶና የቆርቆሮ ስቶክ ካርድ እና በንብረት ያዥ የሚያዘው ቢን ካርድ ባላንስ የሌላቸው መሆኑ፣ መጋዘን ውስጥ ግን ከ 320 በላይ ከረጢት ሲሚንቶ እና ከ 320 በላይ የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች መገኘታቸው፣
- ሲሚንቶዎች እና ብረቶች በንብረት ወጪ ማድረጊያ /Stores Issue Slip/ የሚፈቅደው ኃላፊ ወጪ እንዲደረግ በፊርማው ሳያረጋግጥ ከንብረት ክፍል ወጪ የሚደረጉ መሆኑን፣
- ለሥራ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረጉት እና ወጪ ያልተደረጉ ባለ8፣ ባለ10፣ ባለ12፣ ባለ16፣ ባለ20 ፌሮ ብረቶች በጣም በተቀራረበ ቦታ መለየት በማይቻል ሁኔታ በአንድ ላይ እንዲቀመጡ የተደረገ መሆኑን፣
- ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪ ነዳጅ ከማደያ በሚቀዳበት ወቅት በነዳጅ ዘይትና ቅባት መጠየቂያ ቫውቸር (መተአ 013) የሚፈለገው የነዳጅ መጠን ተገልጾ ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ በቅድሚያ ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪው ነዳጅ እንዲሞላ የሚደረግ መሆኑን፣

- ❖ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ካልብሬት ያልተደረጉ ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚይዙት ትክክለኛ መጠን ያልተረጋገጠ መሆኑን፣
- ❖ ሳይት ላይ አሸዋ፣ ጠጠር እና ሲሚንቶ ወደ ማቡኪያ መኪና (concrete mixer) ሲገባ ሲሚንቶ በሚጨመርበት ወቅት የሲሚንቶ ከረጢት በመቀደድ ሲሚንቶው በመሬት ላይ በመፍሰስ የሚባክን መሆኑን፣

ለማየት ተችሏል፡፡

58. ስለጉዳዩ የድርጅቱ የግድብ፣ መስኖ እና መንገድ ኮንስትራክሽን ንዑስ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ በተፈጥሮው ብክነቶች እንደማይጠፉ ሆኖም ግን ንብረቶች በተቻለ መጥን እንዳይባክኑ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ይገባ እንደነበር፤ ሥራ ላይ ሳይውሉ የተገኙትም ሲሚንቶ እና ቆርቆሮዎች ለሥራው በሚያስፈልገው መጠን መውጣት እንደነበረባቸው ሆኖም አሰራሩ ስህተት ሲለሆነ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም የሚስተካከል እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የቃሊቲ ቅርንጫፍ የሎጂስቲክስ ንዑስ የስራ ሂደት ቡድን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከላይ የተገለጹት የአሰራር ግድፈቶች በድርጅቱ አዲስ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ እየተተገበረ ስለሆነ የሚስተካከሉ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡

59. የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች በንብረት መጋዘን ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የገቢና የወጪ ሰነዶች እንዲሟላላቸው በሚመለከተው ኃላፊ እንዲፈቀዱ ካልተደረገ ለታለመለት ዓላማ በትክክል መዋሉ ካልተረጋገጠ የድርጅቱ ንብረቶች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸው ቀርቶ ለስርቆት፣ ለጥፋት እና ለብክነት እንዲጋለጡ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ

60. የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ብልሽት ሲገጥማቸው የብልሽቱ መንስኤ እየተጣራ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ ተደርጎላቸው በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለጥገና ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው ያልወጡ በቃሊቲ ጋራዥ 383፣ በተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 51 እና በከሰም ግድብ እና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 35

በጠቅላላው 469 የሆኑ የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ከአራት ወራት በላይ የሆናቸው መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው ከተከለሱ የመሳሪያዎችና ተሸከርካሪዎች ፋይል ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በየወሩ ከ175 በላይ የሚሆኑ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ ቢሆንም የጥገና ታሪክ /History Jacket/ የሌላቸው፣ ከመጠገናቸው በፊት የብልሽታቸው መንስኤ ስለመጣራቱ እና ተጠግነው ከወጡ በኃላም በትክክል ስለመጠገናቸው በኢንስፔክሽን ስለመረጋገጡ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣
- ❖ በተንዳሆና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የጥገና ፋይል በናሙና ተመርጠው ሲታዩ የተሽከርካሪዎች ጥገና መጠየቂያ፣ የጥገና ሥራ ትዕዛዝ እና የተቀየሩ የመለዋወጫ እቃ ቅጾች በሚመለከታቸው ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች የማይሞሉ እና የማይፈረሙ መሆኑ፣
- ❖ እንዲሁም ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች በትክክል ስለመጠገናቸው እና ተቀይረዋል የተባሉ መለዋወጫ ዕቃዎች በትክክል መቀየራቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን

ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለጉዳዩ በናሙና የተመረጡት ፕሮጀክቶች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በወቅቱ ጠግነው ለማውጣት የሚፈለጉ የመለዋወጫ እቃዎችን በየዓይነታቸው ዘርዝረው እንዲላክላቸው በተደጋጋሚ ለዋና መ/ቤት የሬድዮ መልዕክት ቢያስተላልፉም በወቅቱ ተገዝተው ያልተላኩላቸው በመሆኑ ለበርካታ ወራቶች በጋራዥ ሊቆሙ መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቃሊቲ ጋራዥ የድርጅቱ አጠቃላይ የጥገና ማዕከል ስለሆነ የጥገና ሥራ የሚፈጀው ጊዜ እንደብልሽቱ ክብደትና ቅለት የሚወሰን ቢሆንም በአብዛኛው የመለዋወጫ እቃ እጥረት በመኖሩ በወቅቱ ጠግኖ ለማውጣት እንቅፋት መሆኑን፣ ድርጅቱ አዲስ መዋቅር ቀርጾ እየተተገበረ ስለሆነ ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ለጥገና ከመግባታቸው በፊት

በእንስፔክሽን ክፍል የብልሽታቸው መንስኤ እየተጣራ እና ተጠግነውም ከወጡ በኃላ በትክክል ስለመጠገናቸው እየተረጋገጠ የሚሰራበት ስርዓት እንደሚጀመር ገልጸዋል፡፡

64. ድርጅቱ ባጠቃላይ ካለው 961 መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች 469 (48.8%) የሆኑት የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በወቅቱ ተጠግነው ከጋራዥ እንዲወጡ ባለመደረጉ ድርጅቱ ለኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ጥገኛ እንዲሆን በማድረግ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እንዲያወጣ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የተሽከርካሪና መሳሪያዎች አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ ድርጅቱ ትርፋማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

ድርጅቱ የተሽከርካሪዎች ስምሪት መመሪያ ያለው መሆኑን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

65. ድርጅቱ የተሽከርካሪ መኪናዎች፣ የማሽነሪዎች እና የግንባታ መሳሪያዎች አጠቃቀም መመሪያ ሊኖረው እና ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም ተገቢው ጥቅም መገኘቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

66. በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በኦፕሬተር እጥረት ምክንያት አንድ ቮልቮ ሎደር፣ ሁለት ኮምፓክተሮች ያለስራ ከአንድ ወር በላይ የቆሙ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. ከዚህም በተጨማሪ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች መስራት ከሚገባቸው ሰዓት /Potential Hour/ በታች እየሰሩ እንደሚገኙ እና የዕለት፣ የሳምንት፣ የወር የስምሪት ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑን ለዋናው መ/ቤት ከቀረበ ሪፖርትና በኦዲት ወቅት ከተደረገ ግምገማ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ የፕሮጀክቱ ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቮልቮ ሎደሩ ለጥገና ጋራዥ እንደገባ ኦፕሬተሩ ፈቃድ ጠይቆ ስለነበር እረፍት እንደተሰጠው በመሃል ሎደሩ ተጠግኖ ከጋራዥ እንደወጣ የመረጃ ክፍተት በመኖሩ አንድ ወር ያህል ሊቆም መቻሉን፣ የኮምፓክተሮች ግን የኦፕሬተር እጥረት ችግር እንደነበርባቸው ለዋና መ/ቤት ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቮልቮ ሎደሩን በኦፕሬተር እጥረት ምክንያት ማቆሙ አግባብነት የሌለው የአሰራር ችግር ቢሆንም የኮምፓክተሮቹ ግን ሊሆን የሚችለው ሥራን እና የሚሰሩ

ኮምፓክተሮችን የማጣጣም ሥራ ስለማይሰራ ያለስራ እንደሚቆሙ ሆኖም ግን ያለስራ የቆሙትን ኮምፓክተሮች ወደ ሌላ ፕሮጀክት መላክ ይቻል እንደነበር ገልጸዋል፡፡

69. በድርጅቱ የተሽከርካሪ መኪናዎች፣ የማሽነሪ፣ የግንባታ መሳሪያዎች እና የነዳጅ አጠቃቀምና ስምሪት መመሪያ ባለመኖሩ አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በኦፕሬተር እጥረት ምክንያት መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ መደረጉ፣ መስራት ከሚገባቸውን ሰዓት /Potential Hour/ በታች እንዲሰሩ እና የሰሩበትን ስዓት በትክክል የሚያሳይ የዕለት፣ የሳምንት፣ የወር የስምሪት ሪፖርት እንዲዘጋጅ አለመደረጉ በድርጅቱ ብልሹ አሰራር እንዲሰፍን ክፍተት ከመፍጠሩም በተጨማሪም ድርጅቱን ለተጨማሪ ወጪ እና ለኪሳራ እንዲዳረግ ያደርጋል፡፡

የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች የሚሰጡት አገልግሎት በየጊዜው እየተገመገመ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ

70. የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች በተቀመጠላቸው የአገልግሎት እድሜ ተመን መሰረት የሚሰጡት አገልግሎት በየጊዜው እየተገመገመ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

71. በተንዳሆ እና በከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) የተገዙት የድርጅቱ ስድስት FAW ገልባጭ መኪናዎች እና አምስት SHANTUI ዶዘሮች አንድ ዓመት ሳያገለግሉ ተበላሽተው የቆሙ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከዚሁ ድርጅት በተጨማሪ ለመግዛት ውል የተገባባቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት በድርጅቱ እየተወሰደ ያለ እርምጃ ካለ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ባለመቻሉ ሁኔታውን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

72. ስለጉዳዩ የፕሮጀክቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለመሳሪያዎቹ እና ለተሽከርካሪዎቹ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን እንዲያቀርቡላቸው በተደጋጋሚ ለዋና መ/ቤት የሬድዮ መልዕክት ሲደረግ አቅራቢው ድርጅት ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) የተጠየቁትን መለዋወጫዎች ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አማራጭ መፍትሔ እየተፈለገ እንደሆነ እንደተገለጸላቸው ገልጸዋል፡፡

73. ይህንኑ በተመለከተ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መሳሪያዎቹን ለድርጅቱ ያቀረበው ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) ለቆሙት መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ መሳሪያዎቹ ማገልገል የሚገባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቆሙ በመሆኑ እና አቅራቢው

ለሚገባጠማቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን የጥገናና የመለዋወጫ አቅርቦት እስካላደረገ ድረስ ሊገዛቸው ውል የተገባላቸውን ተጨማሪ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ለመቀበል እንደማይገደዱ ለአቅራቢው ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) እንደተነገረው ገልጸዋል፡፡

74. አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫ የሌላቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች በመገዛታቸው ተፈላጊውን አገልግሎት ሳይሰጡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት መቆማቸው፣ ድርጅቱን ለተጨማሪ ወጪ እና ለኪሳራ እንዲዳረግ ያደርገዋል፡፡

አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አቀማመጥ እና አወጋገድን በተመለከተ

75. አገልግሎት የማይሰጡ የድርጅቱ ንብረቶች፣ ተሽከርካሪ መኪናዎች፣ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫ እቃዎች እና ኬሚካሎች በአግባቡ ሊቀመጡ እና በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡

76. በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከአገልግሎት የተመለሱ ንብረት ክፍል ተመላሽ መደረግ የነበረባቸው የተለያዩ ውፍረት ያላቸው በርካታ ባለ 8፣ ባለ 10፣ ባለ 14፣ ባለ 16፣ ባለ 20፣ ባለ 30 እና ባለ 32 ፌሮ ብረቶች በየፕሮጀክቶቹ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. ከዚህም በተጨማሪ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርጫፍ መ/ቤት ውስጥ ብዛት ያላቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 185 ዶዘሮች፣ ግሬደሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች፣ ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ጄነሬተሮች፣ ኮምፕረሰሮች፣ መበየጃ ማሽኖች፣ ለጥልቅ ውሃ ጉድጓድ የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ የሲሚንቶ ማቡኪያ ሚክሰሮች፣ ሲሚንቶ መጠቅጠቅያ፣ መሬት መጠቅጠቅያ፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ዲናሞዎች እና ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ በርካታ የኮንስትራክሽን መሳሪያ አካላትና እቃዎች፣ ለድርጅቱ አገልግሎት የማይስጡ መለዋወጫዎች እና ከአገልግሎት የተመለሱ አሮጌ መለዋወጫዎች መጋዘን አጣበው ፣ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. ስለጉዳዩ የፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በየፕሮጀክቶቹ ግቢ ውስጥ ብረቶቹ የሚገኙ መሆኑን በአካባቢው የብረት መመዘኛ ሚዛን ባለመኖሩ ገቢ ለማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከአገልግሎት ተመላሽ የተደረጉ ብረቶች በኪሎ ግራም ተመዝነው

ንብረት ክፍል ገቢ እንዲደረጉ በድርጅቱ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም እስካሁን ተግባራዊ አለመደረጉን ሌሎቹ መሳሪያዎችና እቃዎች እንዲወገዱ ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት የቀረበ ቢሆንም እስካሁን እንዲወገዱ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

79. ንብረት ክፍል ተመላሽ መደረግ የነበረባቸው የተለያየ ውፍረት ያላቸው ብረቶች ገቢ ተደርገው በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ አለመደረጉ ንብረቶቹ እንዲባክኑ እና ብልሹ አሰራር እንዲሰፍን በር የሚከፍት ሲሆን አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የመለዋወጫ እቃዎች እና የግንባታ ቁሳቁሶች አለመወገዳቸው አገልግሎት ለሚሰጡ ንብረቶች የሚውለውን መጋዘን ከማጣበባቸውም በተጨማሪ ድርጅቱ ንብረቶቹን በማስወገድ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ያሳጣዋል፡፡

፫. ድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ከንብረት መዛግብት ከወጪ ቀሪ ጋር የሚታረቅ መሆኑን እና ልዩነት ሲኖር እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ

80. የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርዶች እና ከሂሳብ መዛግብት ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲታረቅ መደረግ እና ልዩነት ሲኖረው ወቅታዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

81. በተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት አመታዊ የንብረት ቆጠራ የሚደረግ እና ከንብረት መዛግብት ጋር የሚመዛዘን ቢሆንም በየአመቱ በተደረገው ቆጠራ በመብለጥና በማነስ የታዩት ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ ቀርበው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. ስለጉዳዩ የየፕሮጀክቶቹ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በቆጠራ ወቅት ልዩነት ለታየባቸው እቃዎች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለዋና መ/ቤት ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም መልስ ስላልተሰጣቸው ፕሮጀክቶቹ በራሳቸው ስልጣን ለማስተካከል የሚቸገሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የቃሊቲ ቅርንጫፍ የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፕሮጀክቶች በራሳቸው መለዋወጫዎችን ስለሚገዙ ለመለዋወጫዎቹ ሌጀር የሚዘጋጀው በፕሮጀክቶቹ በመሆኑ በቆጠራ ወቅት ለሚከሰቱ ልዩነቶች በዋና መ/ቤት ማስተካኪያ እንዲደረግባቸው ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን፣ ነገር ግን ድርጅቱ የመሳሪያዎች አስተዳደር ክፍልን በአዲስ መልክ ስላደራጀ መረጃዎችን በዳታ ቤዝ እንዲያዙ እና

በየፕሮጀክቱ ያሉ ማስተካከያ ለሚያስፈልጋቸው ንብረቶች ጉዳያቸው እየተጣራ የማስተካከያ ስራ ወደፊት እንደሚሰራላቸው ገልጸዋል፡፡

83. ሆኖም የቃሊቲ ቅርንጫፍ የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ፕሮጀክቶች በራሳቸው መለዋወጫዎችን ስለሚገዙ ለመለዋወጫዎቹ ሌጀር የሚዘጋጀው በፕሮጀክቶቹ በመሆኑ በቆጠራ ወቅት ለሚከሰቱ ልዩነቶች በዋና መ/ቤት ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ለማድረግ እንደሚቸገሩ ቢገልጹም የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚከለክላቸው ሁኔታ ባለመኖሩ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ የተደገፉ መሆናቸውን በተመለከተ

84. የድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማግኘትና ለመለዋወጥ እንዲቻል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ሊደራጅና ሊጠበቅ ይገባል፡፡

85. በኦዲቱ በናሙና በተመለከትናቸው በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ ተደግፈው ያልተደራጁ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የመሳሪያዎች አስተዳደር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ ተደግፈው ያልተያዙ መሆኑን፣ ለወደፊቱ ድርጅቱ አዲስ መዋቅር እየተገበረ በመሆኑ መረጃዎች በዳታ ቤዝ እንዲያዙ የሚደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

87. የድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ ካልተደገፉ የሚፈለጉ መረጃዎችን በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማግኘትና ለመለዋወጥ አያስችልም፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

88. የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተልዕኮ ብቃት ያለው የሰው ሀይል እና ዘመናዊ መሳሪያዎች በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ የግድብ ፣ የመስኖና ድሬኔጅ፣ የመጠጥ ውሀ፣ የህንፃ የኃይል ማመንጫ፣ የኤሌክትሮ መካኒካልና ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎች በማከናወን ከአገልግሎቱ ከሚሰበሰበውና ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ተመሳሳይ የልማት ስራዎችን በአገሪቱና በሌሎች አገሮች በማስፋፋት ሀገሪቱን በውሃ ሀብቷ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ተልዕኮውን ለማሳካትም የድርጅቱ የግዢ እና ንብረት አስተዳደር በኢኮኖሚ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች የሚከተሉት የድርጅቱ የግዥና የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ❖ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች
  - ✓ የግዥ ዕቅድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
  - ✓ አልፎ አልፎ ግዥዎች በመከፋፈል እና ከተፈቀደላቸው የግዥ ጣሪያ በላይ የሚፈጸሙ መሆኑ፣
  - ✓ ከሶስት አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ ከአንድ አቅራቢ ብቻ በተገኘ ፕሮፎርማ ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፡፡
  - ✓ ብቸኛ አቅራቢ መሆናቸው በጥናት ሳይረጋገጥ አልፎ አልፎ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፣
- ❖ በተንዳሆና በከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በቼክ ለሚፈጸሙት ክፍያዎች ቼክ የሚዘጋጀው ባሸነፈው አቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያ ስም መሆኑ፣
- ❖ የኪራይ ማሽነሪዎች ላልሰሩበት ሰዓት ክፍያ የሚፈጸም መሆኑ፣
- ❖ የኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎችን ከመጠቀማቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ የማይሰራ መሆኑ፣
- ❖ ፕሮፎርማ የመሰብሰብ እና ግዥን የመፈጸም ሥራ በአንድ ግዥ ባለሙያ፣ ንብረት ገቢ የማድረግ እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ንብረት ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በአንድ ንብረት ያዥ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፣

- ንብረቶች ተገዝተው ሲገቡ በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው መገዛታቸው በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩን፣
- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማን (MAN) ለተባለ ገልባጭ መኪና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጥቶ የተገዛ ባሌስትራ (Leaf Spring) ለመኪናው የማይሆን በመሆኑ ከሁለት አመት በላይ በግምጃ ቤት የተቀመጠ መሆኑ፣
- እቃዎች እንደ እንቅስቃሴያቸው ፍጥነት እና አገልግሎታቸው እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በክምችት ሊያዙ የሚገባቸው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ተለይተው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & maximum Stock Level/ ያልተቀመጠላቸው መሆኑ፣
- በተንዳሆ እና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሚን፣ ብረት እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ከንብረት ክፍል በጥቅል በአንድ ፎርማን ወጪ የሚደረጉ መሆኑን እና ሳይት ላይ ላሉ ሌሎች ፎርማኖች የጠየቁትን ያህል ያለምንም መተማመኛ/ሰነድ የሚታደል መሆኑ፣
- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በንብረት ወጪ ማድረጊያ /Stores Issue Slip/ ወጪ የተደረጉ ንብረቶች መጋዘን ውስጥ የተገኙ መሆኑ፣
    - ✓ ሲሚንቶዎች እና ብረቶች በንብረት ወጪ ማድረጊያ /Stores Issue Slip/ ላይ የፈቀደው ኃላፊ ሳይፈርም ከንብረት ክፍል ወጪ የሚደረጉ መሆኑ፣
    - ✓ ለሥራ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረጉት እና ወጪ ያልሆኑት ብረቶች በጣም በተቀራረበ ቦታ መለየት በማይቻል ሁኔታ በአንድ ላይ እንዲቀመጡ የተደረገ መሆኑ፣
    - ✓ ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪ በነዳጅ ዘይትና ቅባት መጠየቂያ ቫውቸር (መተአ 013) የሚፈለገው የነዳጅ መጠን ተገልጾ ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ነዳጅ እንዲሞላ የሚደረግ መሆኑ፣
    - ✓ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ካልብሬት ያልተደረጉ ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚይዙት ትክክለኛ መጠን ያልተረጋገጠ መሆኑ፣
- በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች በሚገኙ ጋራዥች ለጥገና ገብተው ከአራት ወር በላይ የሆናቸው 469 የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች መኖራቸው፣

- በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በናሙና ተመርጠው ከተከለሱ ለጥገና ጋራዥ የገቡ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ፋይል ውስጥ የጥገና ታሪክ /History Jacket/ የሌላቸው እና ከመጠገናቸው በፊት የብልሽታቸው መንስኤቸው እንዲሁም ከተጠገኑ በኃላ በትክክል ስለመጠገናቸው በኢንስፔክሽን የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- በተንዳሆና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በናሙና ተመርጠው በታዩ ለጥገና ጋራዥ የገቡ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የጥገና ፋይል ውስጥ የጥገና መጠየቂያ፣ የጥገና ሥራ ትዕዛዝ እና የተቀየሩ የመለዋወጫ እቃዎች ቅጽ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች የማይሞሉ እና የማይፈረሙ መሆኑ፣
- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በኦፕሬተር እጥረት ምክንያት አገልግሎት መስጠት እየቻሉ አንድ ቮልቮ ሎደር፣ ሁለት ኮምፓክተሮች ያለስራ ከአንድ ወር በላይ የቆሙ መሆናቸው፣
- በተንዳሆ እና በከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) የተገዙት ስድስት FAW ገልባጭ መኪናዎች እና አምስት SHANTUI ዶዘሮች አንድ ዓመት ሳያገለግሉ ተበላሽተው የቆሙ መሆናቸው፣
- በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከአገልግሎት የተመለሱ ንብረት ክፍል ተመላሽ ያልተደረጉ የተለያየ የውፍረት መጠን ያላቸው በርካታ ባለ 8፣ ባለ 10፣ ባለ 14፣ ባለ 16፣ ባለ 20፣ ባለ 30 እና ባለ 32 ፌሮ ብረቶች በየፕሮጀክቶቹ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ዶዘሮች፣ ግሬደሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች፣ ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ በርካታ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች፣ ጄነሬተሮች፣ ኮምፕረሰሮች፣ መበየጃ ማሽኖች፣ ለጥልቅ ውሃ ጉድጓድ የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ የሲሚንቶ ማቡኪያ ሚክሰሮች፣ ሲሚንቶ መጠቅጠቅያ፣ መሬት መጠቅጠቅያ፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ዲናሞዎች፣ ለተለያዩ ግንባታ መሳሪያዎች የሚያገለግሉ በርካታ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችና ተሽከረካሪዎች አካላት እና ለግንባታ ሰራ የሚያገለግሉ በርካታ እቃዎች በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ለድርጅቱ አገልግሎት የማይውሉ መለዋወጫዎች እንዲሁም ከአገልግሎት የተመለሱ አሮጌ መለዋወጫዎች መጋዘን አጣበው የተቀመጡ መሆኑ፣

- ❖ በተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት አመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በየአመቱ በተደረገው ቆጠራ በመብለጥና በማነስ የታዩት ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ ቀርበው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ❖ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ እና ንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ እንዲታገዙ ያልተደረገ መሆኑ፣

ታውቋል።

89. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

90. የድርጅቱ ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ፣ ተመጋጋቢ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር እና የድርጅቱ የግዢ እና ንብረት አስተዳደር በመመሪያ መሰረት እንዲፈጸም የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡-

- ❖ ድርጅቱ ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት በቅድሚያ የግዥ እቅድ በማዘጋጀት የዋጋ ቅናሽና የጥራት ተጠቃሚ የሚያደርገውን የግዥ ስልት በመለየት ግዢ መፈጸም ይኖርበታል፡፡
- ❖ ድርጅቱ በግዢ ዕቅዱ መሰረት በጥቅል ወይም በቅንጅት ሊገዙ የሚገባቸው ግዥዎችን በመለየት በጥቅል መግዛት ይገባዋል፡፡
- ❖ ድርጅቱ በቼክ ክፍያ ሲፈጽም ቼክ ባሸነፈው አቅራቢ ድርጅት ስም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቱ በፕሮፎርማ ግዥ ሲፈጽም በአቅራቢዎች ዘንድ የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዲኖር እና በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው አቅርቦት ለማግኘት እንዲቻል ብቸኛ አስመጪዎችን እና ሌሎች ህጋዊ ፈቃድ እና እውቅና ያላቸውን ድርጅቶች በመለየት በግዢ መመሪያው መሰረት ቢያንስ ከሶስት ድርጅቶች ፕሮፎርማ ሰብስቦ በማወዳደር ግዢ ሊፈጽም ይገባል፡፡
- ❖ የግዥ ኘሮፎርማ መሰብሰብ እና ግዥውን የመፈጸም ሥራ፣ ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ ገቢ የማድረግ እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እና ንብረቶቹን ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቱ ለኪራይ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች የሚያወጣው ወጪ አዋጭ መሆኑ በቅድሚያ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ተሰርቶ ሊረጋገጥና በሚመለከተው የሥራ ክፍል ሊወሰን ይገባል፡፡ ከኪራይ መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ በቅርብ ኃላፊው ክትትል በማድረግ በየወሩ ትክክለኛ የሆነ ሪፖርት ለዋና መ/ቤት ሊደርስ የሚችልበትን ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኛቸውን ቋሚና አላቂ እቃዎች በእስፔሲፊኬሽናቸው መሰረት መሆናቸውን ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት /ባለሙያዎች/ እየተረጋገጠ ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በድርጅቱ የሚገኙ ዕቃዎች በአቀማመጥ እና አያያዝ እንዳይበላሹና በሰው ልጅ ጤንነት እና በአካባቢ ላይ ችግር እንዳያስከትሉ እንደ እንቅስቃሴያቸው ፍጥነት፣ አዲስ፣ የሚያገለገሉ፣ የማያገለግሉ፣ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ መደረግ አለበት፡፡ በክምችት የሚያዙ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ተለይተው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & Maximum Stock Level/ ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡

- የድርጅቱ ንብረቶች ገቢና ወጪ ሲደረጉ የገቢና የወጪ ሰነዶች ሊሟላላቸው እና በሚመለከተው ኃላፊ እንዲጸድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት አስፈላጊው የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ለድርጅቱ ተበላሽተው ያለሥራ ጋራዥ የቆሙት 469 ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የብልሽታቸው መንስኤ እየተጣራ ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ ወይም ሥራ ላይ ሊውሉ የማይችሉ ከሆነ በባለሙያ ተጠንቶ በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ እና የግንባታ መሳሪያዎች የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ ሊያዘጋጅና እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በድርጅቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መለዋወጫዎች እና የግንባታ ቁሳቁሶች በባለሙያ ተጠንቶ በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ በየአመቱ በሚያደረገው የንብረት ቆጠራ በማነስም ሆነ በመብለጥ ለሚታዩ ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ እየቀረበ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

- የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች ለቁጥጥር እና ክትትል እንዲያመች፣ መረጃዎች በቀላሉ ለመለዋወጥ እንዲያስችል፣ ለድርጅቱም ሆነ ለሶስተኛ ወገን በወቅቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በዘመናዊ ተክኖሎጂ ሊደገፉ ይገባል፡፡

91. በመጨረሻም የውሃ ሥራዎችና ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት እንዲሁም በናሙና የታዩ የድርጅቱ ፕሮጀክቶች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1፡ <u>ድርጅታዊ መዋቅር</u>



አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
በድርጅቱ የግዢ ስርአት/አፈፃፀም የግዢ መመሪያን ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤	1. የድርጅቱ የግዥ አስተዳደር መመሪያ ከመንግስት ግዥ መመሪያ ጋር የማይጣረስ እና በየወቅቱ ወቅወታዊ/Update/ ሊደረግ ይገባል፡፡
	2. ከስራ ሂደት ክፍሎች እና ከፕሮጀክቶች የተሰበሰበው የእቃዎች የአገልግሎቶች የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እና የምክር አገልግሎቶች መሰረት ያደረገ በጀት ተዘጋግቶ እንዲጸድቅ መደረግ አለበት ፡፡
	3. በዋናው መ/ቤት፣ በቃሊቲ (ቅርንጫፍ)፣ በፕሮጀክቶችና ሌሎች ግዥን እንዲያከናውኑ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች ግዥን ሲፈጽሙ በወቅቱ የተፈለገውን ግዥ ለማከናወን፣ የዋጋ ቅናሽና የጥራት ተጠቃሚ የሚያደርገውን የግዥ ስልት በመለየት ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት የግዥ እቅድ በቅድሚያ በማዘጋጀት አገልግሎት ላይ ማዋል ይገባቸዋል፡፡
	4. እያንዳንዱ ተጠቃሚ የግዥ ፍላጎቱን በዕቃ መጠየቂያ ሰነድ ሞልቶ ከአስፈላጊ መግለጫ ጋር አያይዞ በጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ላይ ለንብረት ቁጥጥር ባለሙያ እንዲደርስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
	5. በድርጅቱ የንብረት ጥያቄ ሲቀርብ ለጥያቄዎቹ ግዢ እንዲከናወን ከመደረጉ በፊት የተጠየቁት ንብረቶች በንብረት ግምጃ ቤት በሚፈለገው መጠን፣ ዓይነት እና ጥራት አለመኖሩ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	6. ድርጅቱ የአቅራቢዎችን ዝርዝር እና የአቅርቦት ታሪክ በአግባቡ እየመዘገበ ሊይዝ ይገባል፡፡
	7. ግዥ የሚፈጸመው በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡ ድርጅቶች መሆን አለበት፡፡
	8. በጥቅል ወይም በቅንጅት መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ዓይነቶችን በመለየት በቅንጅት እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	9. በድርጅቱ የሚፈፀሙ ግዢዎች በድርጅቱ የግዢ መመሪያ ላይ በተጠቀሱት የግዢ ስልቶች ሆኖ የግዥ ስልቱ የተመረጠበት ምክንያት በድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ ሊጸድቅ ይገባል።
	10. በድርጅቱ ግዥን የሚፈቅዱና የሚያጸድቁ በግዥ መመሪያ መሰረት ሥልጣን የተሰጣቸው ኃላፊዎች የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲልኩ ኮፒዉም ለንብረት ክፍል፣ ለግዥ ክፍል እና ለመሳሰሉት ክፍል ሊደርስ ይገባል።
	11. ድርጅቱ የጨረታ ሰነዱን ሲያዘጋጅ በግዢ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች ሊያካትት ይገባል።
	12. በድርጅቱ የሚፈፀም ማንኛውንም የኮንትራት ግዥ ከመፈጸሙ በፊት ግዥው የሚያስገኘው ጠቀሜታ ተተንትኖ በዝርዝር ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ ሊጸድቅ ይገባል።
	13. የፕሮፎርማ ግዥ ለመፈጸም ሲባል በጥቅል ሊገዙ የሚገባቸው ግዥዎችን ከፋፍሎ መግዛት አይገባም።
	14. በድርጅቱ የግዥው ጥያቄ በዕቅድ ሳይያዝ በአጣዳፊ ሥራ ምክንያት የቀረበ ከሆነ ግዢው ከመከናወኑ በፊት ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ አስፈጻሚ፣ የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም የፕሮጀክቱ የሥራ ሂደት ባለቤት ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ ይኖርበታል።
	15. በድርጅቱ በልዩ ሁኔታ የሚፈጸመው ግዢ አስገዳጅና አስቸኳይ ሆኖ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከአራት ጊዜ መብለጥ የለበትም።
	16. ድርጅቱ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ከመከራየቱ በፊት አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis ይገባል።
	17. ድርጅቱ በኪራይ የሚጠቀምባቸው መሣሪይዎችና ተሽከርካሪዎች ያከናወኑት የስራ መጠን እና ሰዓት ከወጪው ጋር ሊነጻጸር እና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል።
	18. ከኪራይ መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ በቅርብ ኃላፊው ክትትል ሊደረግና በየወሩ ለዋና መ/ቤት

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡
	19.ኘሮፎርማ መሰብሰብና ማጠቃለያ ወይም ግምገማ የማከናወን፣ ግዥን ማከናወንና ርክክብ የማድረግ፣ የገቢ ደረሰኝ የማዘጋጀትና ሰነድ የማረጋገጥን እንደአግባብነታቸውና የጠቀሚታ ደረጃቸው እየታየ ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰዎች እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡
የንብረት አያያዝን እና አጠቃቀምን ለመቆጣጠር ፣ለመከታተል እንዲሁም በወቅቱ ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤	20.ድርጅቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኛቸውን ቋሚና አላቂ እቃዎች በእስፔፊኬሽናቸው መሰረት በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ በማድረግ አስፈላጊው ምዝገባ ሊከናወንላቸው ይገባል፡፡
	21.የድርጅቱ ዕቃዎች እንደእንቅስቃሰያቸው ፍጥነት፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው ሊያዙና ሊቀመጡ ይገባል፡፡
	22.የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች በንብረት መጋዘን ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የገቢ ሰነዶች ሊሟላላቸውና እና ወጪም ሲደረጉ የንብረት ወጪ መጠየቅያ ቀርቦ በሚመለከተው ኃላፊ ሊፈቀድ ይገባል፡፡
	23.በድርጅቱ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በክምችት ለሚያዙ እና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ላላቸው ንብረቶች /ዕቃዎች ዝቅተኛ የክምችት መጠን /Minimum Stock Level/ እንዲቀመጥላቸው ሊደርግ እና በዚያ መሰረትም የንብረቶች/ እቃዎች ክምችት ተግባራዊ እንዲደረግ ሊሆን ይገባል፡፡
	24.በንብረት መጋዘን ውስጥ የሚከማቹ ማንኛውም የድርጅቱ ንብረቶች ወደ ጥቅም ላይ የሚውሉት ጊዜ ሊታወቅ እና በተቀመጠውም ጊዜ መስረት ለተባለለው ዓላማ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡
	25.የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች በተቀመጠላቸው የአገልግሎት እድሜ ተመን መሰረት የሚሰጡጥ አገልግሎት በየጊዜው ሊገመገምና በግምገማውም መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	26.ወደ ፕሮጀክቶች ለሚላኩ ዕቃዎች የዲስፓች መረጃ በአግባቡ ሊሞላና የተላከላቸውም ፕሮጀክቶች በትክክል ንብረቶችቹን ቆጥረው ስለመቀበላቸው ማስረጃ ሊልኩ ይገባል፡፡
	27.በነዳጅ የሚሰሩ የድርጅቱ ማሽነሪዎች በስዓት እንዲሁም ተሽከርካሪዎች በክሎሜትር ምን ያህል ነዳጅ እንደምጠቀሙ ሊታወቅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	28.የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እንዲቻል ሲበላሹ የብልሽታቸው መንስኤ እየተጣራ አስፈላጊው ጥገና ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
	29.የመድህን ዋስትና ለሚያስፈልጋቸው የድርጅቱ ንብረቶች የመድህን ዋሰወትና ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	30.ድርጅቱ የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ፣ የግንባታ መሳሪያዎች፣ እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊኖረው እና ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡
የንብረት አወጋገድ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤	31.የድርጅቱ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ላይ በሚውሉበት ወቅት ከሚያስገኙት ጥቅም ይልቅ የሚያስወጡት ወጪ የሚበልጥ መሆኑ ከተረጋገጠ በድርጅቱ አወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡
	32.አገልግሎት የማይሰጡ የድርጅቱ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መለዋወጫዎች እና ኬሚካሎች በአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡
	33.ከሽያጭ ውጪ በማቃጠል እና በመቅበር የሚወገዱ ንብረቶችን ለመለየት የሚረዳ መመሪያ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	34.ንብረቶችን ከማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በህጋዊ ደረስኝ ለድርጅቱ ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡
	35.የተወገዱ የድርጅቱ ንብረቶች ከመዝገብ ሊሰረዙ ይገባል፡፡
በድርጅቱ የግዥ	36.ማንኛውም የግዢ እና ከግዢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችና

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
እንዲሁም የንብረት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤	መረጃዎች በእያንዳንዱ ግዥ ቅደም ተከተል ተለይቶ ለብልሽትና ለጥፋት ሊዳረጉ በማይችሉበት ቦታ ፋይል መደረግ ይገባል፡፡
	37.በድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደርን መረጃዎች በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማግኘት እንዲቻል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሊደገፍ ይገባል፡፡
	38.ድርጅቱ ያሉትን መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ብዛትና ያሉበትን አቋም ለመከታተል የሚያስችል ምዝገባ ሊያካሂድ እንዲሁም ለእያንዳንዱ መሳሪያና ተሽከርካሪ ፋይል ሊያዘጋጅና አጠቃላይ ታሪክ እየተመዘገበ ሊይዝ ይገባል፡፡
	39.በድርጅቱ ውስጥ ግዥን እንዲያከናውኑ ሃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል ስለግዥ እቅድ ክንውን ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና የዓመት ግዢ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	40.የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርዶች እንዲሁም ከሂሳብ መዛግብት ጋር እንዲታረቅና ልዩነት ቢኖር ወቅታዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡